# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ  ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት

# የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ

# ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት/2016
አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጄክት ጽሕፈት ቤት
# የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጄክት ጽሕፈት ቤት የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጄክት ጽሕፈት ቤት ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

**ኦዲታችን፡-**

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጄክት ጽሕፈት ቤት ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በፕሮጄክ/*ት ጽሕፈት ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የ2015 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት በጽ/ቤቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል።

I. ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

## II. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (Emphasise Matters)

1.1 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8ተ.ቁ1/ሀ በጥሬ ገንዘብ እና በቼክ ለተሰበሰበ ገንዘብ በሚኒስቴሩ ፈቃድ የታተመ ተከታታይ ቁጥር የተሰጠውና ሴሪ ያለው ሕጋዊ የገቢ ደረሰኝ መስጠት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በ2015 በጀት ዓመት ከሰራተኛ የደመወዝ ቅጣት ተቀናሽ የተደረገ በሂሳብ አርእስት 1451199 (ልዩ ልዩ ገቢዎች) ብር 1,842.00 በሪፖርት በገቢ ተመዝግቦ የሚታይ ሲሆን ባንክ ገቢ ለመሆኑ የባንክ ሲሊፕ (Deposit slip) እና የገቢ ደረሰኝ (RV) ያልተቆረጠለት መሆኑ፣

1.2 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 ንዑስ ክፍል 8 ተራ ቁጥር 2ለ የወጪ ሂሳብ አያያዝ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለ ወጪው የተሟላ መቅረብ ሥልጣና ባለው አካል ሊፈቀድ እንዳበት ይገልጻል፡፡ በbመሆኑም ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤቱ የአባይ ግድብ 12ኛ አመት መታሰቢያ አስመልክቶ ባዘጋጀው ዝግጅት ላይ የምሳ የመስተንግዶ አገልግሎት እንዲሰጥለት ከአካለ ምህረቱ ባርና ሬስቶራንት ጋር በሚቀርብ ማስረጃ በ1ሰው 299.99 ብር ለመክፈል ውል ተዋውሎ በቀን 26/10/2015 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 3072 የ220 ሰዎች ሂሳብ ብር 65,999.86 ለአቅራቢው ከፍሏል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ውስጥ በቀረበው ማስረጃ መሰረት መስተንግዶውን የተጠቀሙ ተሳታፊዎች ብዛት 124 በመሆኑ ብር 37,198.76 መክፈል ሲገባ ለድርጅቱ በብልጫ ለተከፈለው ብር 28,799.04 የተሳታፊዎች የሰዓት መቆጣሪያ ፊርማ (የአቴንዳንስ) በደጋፊ ማስረጃነት ያልቀረበ መሆኑ፣

1.3 በፌዴራል መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 ክፍል 7 አንቀፅ 28 ንኡስ አንቀፅ 28.3 የውል አስተዳደር በሚል ስር የመንግስት መ/ቤቶች ውሉን ተፈፃሚ ለማድረግ በአቅራቢው ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት በመለየት አቅራቢው በውሉ መሰረት ተግባራቱን በወቅቱ መፈፀሙን ተከታትለው ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ንብረትነቱ የቤተ መዛግብትና ቤተመፃሕፍት ኤጀንሲ የሆነ ጄነሬተር ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኤሌክትሪክ በጠፋ ጊዜ የጄኔሬተር የነዳጅ ወጪ 15% ናፍጣ በመሙላት በኤጀንሲው ጄነሬተር እንዲጠቀም በ2007 ዓ/ም ውል

በመፈራረሚቸው በውሉ መሰረት በዓመት ሁለት ጊዜ (600 ሊትር *2 = 1,200 ሊትር) ናፍጣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 00004451 (600 ሊትር×49.02 ብር) 29,412.00 ብር እና በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 00005265 (600 ሊትር×71.08 ብር) 42,648.00 ብር በአጠቃላይ ድምር 72,060.00 ብር ወጪ አውጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በውሉ መሰረት የሚከፈለው የጄነሬተር የናፍጣ ወጪ በትክክል የወጣው የናፍጣ ወጪ 15% መሆኑ የሚረጋገጥበት መንገድ የሌለ መሆኑ፣
- የተሞላው ናፍታ ኤጀንሲው ለመቀበሉ የሚገልፅ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የማይቀርብ መሆኑ፣

1.4 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ተራ ቁጥር 3 የሂሳብ አወቃቀር ስርአት በሚለው ስር የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች በየሂሳብ መደባቸው ተለይተው መመዝገብ እንዳለባቸው መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች የተመዘገቡ በድምሩ ብር 169,937.24 የወጪ ሂሳቦች መደባቸውን ያልጠበቀ ምዝገባ መሆኑ፣

1.5 የማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ከግንቦት 16/2013 ጀምሮ ከኪራይ ቤቶች ቢሮ የተከራየ ሲሆን ቢሮው ውስጥ ሳይገባና ላልተገለገለበት የቤት ኪራይ በድምሩ ብር 6,570,664.70 የከፈለ መሆኑ፣

1.6 የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል 5 አንቀፅ 17 የተመርማሪዎች ግዴታ ተራ ቁጥር 1 ላይ የፌዴራል ዋና ኦዲተር ፣ የመ/ቤቱ ኦዲተሮች ወይም የፌዴራል ዋናው ኦዲተር ወኪሎች ለምርመራ ጠቃሚና አስፈላጊ የሚመስሏቸውን መፅሀፍት ፣ መዘክሮች ፣ መዝገቦች ፣ ሰነዶችና ሌሎች የፅሁፍ እና የቃል መረጃዎች ሁሉ ሲጠይቁ የተጠየቀው ግለሰብ ፣ ሰራተኛ ወይም ባለስልጣን በትክክልና በተሟላ አኳኋን ወዲያውኑ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት አዋጁ ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤቱ ለውሎ አበል በቀን 30/10/2015 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 5530 ብር 6,030.00 እና በቀን 30/10/2015 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 5529 ብር 5,770.00 በድምሩ ብር 11,800.00 በወጪ ለመዘገበው ሂሳብ ሰነዶቹ እንዲቀርቡልን በተደጋጋሚ ብንጠይቅም ያልቀረበ መሆኑ፣

1.7 የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል። በዚሁ መሰረት ጽህፈት ቤቱ በጀቱን የሚቆጣጠር መሆኑን ለማረጋገጥ ለ2015 በጀት ዓመት በየበጀት ፕሮግራሞቹ ለየሂሳብ ኮዶቹ የተፈቀደው የወጪ በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ፡-

መደበኛ በጀት በ16 የሂሳብ መደቦች ብር 1,474,830.31 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤

2 <u>**የህጋዊነት ጉዳዮች (Compliance Matters)**</u>

2.1 በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 በተቀመጠው አንቀጽ 91 ንዑስ ቁጥር 1 የግብር ከፋዩ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የግብር ክፍያ መለያ ቁጥርን ያላቀረበ እንደሆነ ግብር ቀንሶ የሚያስቀረው መ/ቤት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ 30% ቀንሶ ለገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ማድረግ እንዳለበት በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ የማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤቱ በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ በተካሄደው የአባይ ዘመን ትውልድ ታላቅ የስነ-ፅሁፍ ፕሮግራም ላይ ስራቸውን ላቀረቡ ባለሙያዎች የሙያ ክፍያ የከፈለ ሲሆን በአዋጁ መሰረት የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ካላቀረቡ 30% ቆርጦ ለገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ማድረግ ሲገባ በድምሩ ብር 10,188.00 ገቢ ያላደረገ መሆኑ፤

2.2 በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ/2002 ክፍል 5 በአንቀፅ 24.3 ላይ የመንግስት መ/ቤት በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ሲፈፅም በውድድሩ ተሳታፊ የሚሆኑ አቅራቢዎች ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የሚመረጡ ሆኖ ቁጥራቸው ከ 3 ማነስ እንደሌለበት በመመሪያው ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ መስተባበሪያ ጽሕፈት ቤቱ ፕሪንተር በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ሲፈፅም ከ 3 ያላነሱ ድርጅቶችን በማሳተፍ መሆን ሲገባ 2 ድርጅቶችን ብቻ በማወዳደር በቀን 29/08/2015 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 5253 ብር 297,000.00 ለአሸናፊ ድርጅቱ ለናሽናል ማርኬተር ክፍያ የፈፀመ መሆኑ፤

2.3 በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ/2002 ክፍል 5 በአንቀፅ 24.8 ላይ የመንግስት መ/ቤት በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፅምባቸው ግዥዎች በኤጀንሲው ድህረ-ገፅ የሚወጣውን ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር በግዥ የስራ ክፍሉ የሚካሄድ የገበያ ጥናትን በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ

ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባ በመመሪያው ተገልጿል፡፡ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤቱ በተለያዩ ቀናቶችና የውጪ ማስመስከሪያ ቁጥሮች በድምሩ በብር 1,716,478.00 የገበያ ጥናት ሳይደረግ የተፈፀመ ግዥ መሆኑ፤

2.4 በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ/2002 ክፍል 8 ንዑስ አንቀፅ 33.1 የአቅራቢ ምዝገባ በሚለው ስር በማንኛውም የመንግስት ግዥ ለመሳተፍ በአቅራቢነት መመዝገብ ግዴታ መሆኑን ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ጽሕፈት ቤቱ በተለያዩ ቀናቶችና የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥሮች በድምሩ ብር 565,405.64 ግዥው በመንግስት የአቅራቢነት ዝርዝር /Supplier List/ ውስጥ ከሌሉ ድርጅቶች የተፈፀመ መሆኑ፤የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል ሶስት የስቶክ አስተዳደር ስርዓት ስቶክን ስለመቀበል በሚለው ስር የዕቃ ግምጃቤት ኃላፊው የዕቃውን ትክክለኛነት ከተሰጠው ትዕዛዝ የዕቃ ዝርዝር (specification) ጋር በማመሳከር ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ በድምሩ ብር 799,133.01 ግዥው በናሙናው መሰረት የተፈፀመ ለመሆኑ ከጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴዎች ማስረጃ ሳይቀርብ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገ መሆኑ፤

2.5 ለጽ/ቤቱ ሰራተኞች ውሎ አበል ሲከፍል በመንግሥት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል መመሪያቁጥር 3 /2012 ዓ.ም መሆኑ ሲጣራ በክልል ዋና ከተማ አስተዳደርና በከተማ አስተዳደር የውሎ አበል መጠን ብቻ በማስላት በድምሩ ብር 48,437.17 የተከፈለ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት በተንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች የተከፈለውን የቁርስ የምሳ እራት አበል ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ቦታው በዝርዝር ባለመገለጹ የውሎ አበል ክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋጋጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

2.6 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 /4 ፊደል መ የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሆኖም ብር 82,468.60 ተሰብሳቢ ሂሳብ ማስረጃ ያልቀረበለትና ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

## 3. ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

### 3.1 የንብረት አያያዝን በተመለከተ

**የአላቂ እና ቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት**

- በዕቃ ግምጃ ቤቱ ውስጥ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ፣ ያገለገሉ እና አዳዲስ ንብረቶች ፣ መወገድ ያለባቸው ዕቃዎች በአንድ ላይ ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑ፣
- የአገልግሎት ጊዜያቸው እንደ እ.ኤ.አ በ22/09/2020 ያበቃ ሳኒታይዘሮች ብዛት 38 ፍሬ ሳይወገዱ በዕቃ ግምጃ ቤቱ ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- የንብረት የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው በ2014 ዓ.ም ወደ ዕቃ ግምጃ ቤቱ የገቡ ቲሸርቶች ብዛት 307 አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የተቀመጡ መሆኑ፣
- የፎቶ ኮፒ ማሽኖች ብዛት 3 ተጠግነው አገልግሎት ላይ ሳይውሉ ከ2 ዓመት በላይ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ እና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያየ ሞዴል ያላቸው ፕሪንተሮች ብዛት 13 ፣ ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮች ከነአክሰሰሪያቸው ብዛት 16 ተቀላቅለውና ተደራርበው ከ 1 ዓመት እስከ 3 ዓመት ድረስ የተቀመጡ መሆኑ፣ የማይሰሩ ዲቫይደሮች ብዛት 19 ሳይወገዱ ከ 3 አመት በላይ በዕቃ ግምጃ ቤቱ ውስጥ ያሉ መሆኑ፣
- ከ 2 አመት በላይ የመኪና ቴፖች ብዛት 2 በብልሽት ምክንያት የተቀመጡ መሆኑ፣
- 1 ኒኮላ ካሜራ ፣ 20 ሜትር አቡጀዲ ጨርቅ ፣ 9 የወንዶች ሸሚዞች ያለ አገልግሎት የተቀመጠ መኖሩ፣
- በ2014 ዓ.ም ተገዝቶ የገባ REXMARK TONNER 410 ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆኑ፣
- በ2013 ዓ.ም ተገዝተው የገቡ 50 የፕላስቲክ መጥረጊያዎች ፣ 33 የዘንባባ መጥረጊያዎች ጥቅም ላይ እየዋሉ አለመሆኑ፣
- በ2010 ዓ.ም ተገዝቶ ከገባው 250,000 የደረት ፒን ውስጥ 96,087 የሽያጭና የስጦታ የወጪ እንቅስቃሴው አጥጋቢ ባለመሆኑ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፣
- አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የተበላሹ ባለ 4 ሊትር መጠን ያላቸው 2 የቤት ማስዋቢያ የግድግዳ ቀለሞች ሳይወገዱ ረጅም ጊዜ የተቀመጡ መሆኑ፣

- በ2012 ዓ.ም ኮሮና በሽታ ወረርሽንን ለመከላከል አልኮል የመጣባቸው 5 መካከለኛ የፕላስቲክ በርሜሎች ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ለተሽከርካሪዎች ማጠቢያ ተብሎ በ2013 ዓ.ም ተገዝቶ የገባ 40 ሜትር የውሀ ማስተላለፊያ ጎማ ወጪ ሳይደረግ የተቀመጠ መሆኑ፣
- በ2008 ዓ.ም ተገዝተው የገቡ GPR-18 የፎቶ ኮፒ ማሽኖች ብዛት 14 በአሁኑ ሰዓት ቀለሞቹን የሚጠቀሙ ማሽኖች ባለመኖራቸው በሚል ያለመፍተሄ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በ2014 ዓ.ም ተገዝተው የገቡ 1 CD Drive External እና 1 እስፒሊተር ቋሚ ዕቃዎች ለጠየቀው ክፍል ወጪ ተደርገው ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በ2010 ዓ.ም በልገሳ የመጣ 1 ላፕቶፕ ኮምፒተር አገልግሎት ላይ ያልዋለ መሆኑ፣
- 10 ተመላሽ ላፕቶፖች ጥቅም ላይ ሳይውሉ የተቀመጡ መሆኑ፣
- እጅግ ብዛት ያላቸው የወረቀት መጠረዣ እሪንጎች ጥቅም ላይ ሳይውሉ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ከ2011 ዓ.ም በፊት ተገዝቶ የገባ ትልቁ በቻርጅ የሚሰራ የእጅ ባትሪ ብዛት 5 አገልገሎት ላይ ሳይውል የተቀመጠ መሆኑ፣
- ከ2013 ዓ.ም በፊት ተገዝተው 9 የወንዶች ሸሚዞች አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የተቀመጡ መሆኑ፣

<u>የልገሳ ዕቃዎች ማስቀመጫ ግምጃ ቤት ውስጥ የተቀመጡ</u>

- ተሸጠው ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ይውሉ ዘንድ ከተለያዩ ድርጅቶች በ2010 ዓ.ም በልገሳ ወደ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤቱ የገቡ አልፋ የልብስ ማጠቢያ ማሽን ብዛት 42 ፣ ሀይሰንስ ፊሪጅ ብዛት 10 ፣ ሀይሰንስ ዲፕ ፍሪጅ ብዛት 2 ፣ ቤኮ ፍሪጅ ብዛት 2 እና ፋና ቴሌቪዥን 32 ኢንች ብዛት 2 ተሸጠው ለግድቡ ግንባታ መዋል ሲገባቸው ሳይሸጡ የተቀመጡ መሆናቸው፡፡

<u>የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት</u>

- ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ያልተወገዱ ተመላሽ የተሽከርካሪ ጎማዎች ብዛት 68 ፣ የመኪና ባትሪዎች ፣ ተመላሽ የተሽከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃዎች ፣ ተመላሽ የመኪና ወንበሮች ልብሶች ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑ፤
- ተመላሽ ተሽከርካሪ ወንበር ብዛት 1 ፣ ኖርማል ወንበሮች ብዛት 7 እና አዳዲስ ወንበሮች ብዛት 3 አላግባብ የተቀመጡ መሆኑ፣

- ከ2012 ዓ.ም በፊት በግዥ የገቡ 2 የሞተር ሳይክል ጎማዎች አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ከ2010 ዓ.ም በፊት በግዥ የገቡ የተለያዩ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች ዕቃዎቹን የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች ስሌለሉ በሚል ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣
- ከ2011 ዓ.ም በግዥ የገቡ የአይሲቲ መስመር ዝርጋታ ማስተላለፊያ የግድግዳላይ ኮንዲቶች ብዛት ከ200 በላይ አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የተቀመጡ መሆኑ፣

**3.2. የወሰዷቸውን ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች ሳያስረክቡ የለቀቁ ሰራተኞችን በተመለከተ**

ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤቱ ለሰራተኞች ለስራ ማስፈፀሚያ ተንቀሳቃሽ ቋሚ ዕቃዎችን ሲሰጥ ዋስ እንዲያቀርቡ ማድረግ ሲገባ ባለማድረጉ ጽ/ቤቱን የለቀቁ ሰራተኞች ለስራ ማስፈፀሚያ የወሰዷቸውን **ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች ተመላሽ ሳያደርጉ በመልቀቃቸው ጽ/ቤቱ የብር** 70,546.69ዋጋ ያላቸው ንብረቶችን ያጣ መሆኑን በኦዲታችን አረጋግጠናል፡፡

3.3 ባለፉት በጀት ዓመታት የኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ እርምጃ የወሰደባቸው መሆኑ ሲጣራ፡

**የ2011 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች**

- በድምሩ ብር 117,925.45 ያለአግባብ ውሎ አበል ክፍያ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት**

**መጋቢት የካቲተት/ 2016**